**<u>በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት የተዘጋጀ የ2016ዓ.ም የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት የ6ኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርት ሞዴል ፈተና</u>**

1. 0.785 ወደ መቶኛ ሲለወጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

    ሀ) 78% ለ) 87% ሐ) 85.5% መ) 78.5%

2. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ በ7 ተካፋይ የሆነው የትኛው ነው?

    ሀ) 812 ለ) 2214 ሐ) 1214 መ) 281

3. ሙሉ ቁጥር 867መ41 ይህ ሙሉ ቁጥር በ9 ተካፋይ እንዲሆን በፊደል "<u>መ</u>" ቦታ ሊገባ የሚችለው ባለአንድ ሆሄ ቁጥር የቱ ነው?

    ሀ) 0 ለ) 9 ሐ) 1 መ) 3

4. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክል **<u>ያልሆነው</u>** የትኛው ነው?

    ሀ) አንድ ሙሉ ቁጥር በ10 ተካፋይ ከሆነ በ5 ተካፋይ ነው፡፡

    ለ) አንድ ሙሉ ቁጥር በ3 ተካፋይ ከሆነ በ9 ተካፋይ ነው፡፡

    ሐ) አንድ ሙሉ ቁጥር በ8 ተካፋይ ከሆነ በ4 ተካፋይ ነው፡፡

    መ) አንድ ሙሉ ቁጥር በ9 ተካፋይ ከሆነ በ3 ተካፋይ ነው፡፡

5. $5\frac{1}{100}$% ወደ አስርዮሻዊ ቁጥር ሲቀየር ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

    ሀ) 0.0501 ለ) 5.01 ሐ) 50.1 መ) 0.501

6. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል እውነት **<u>ያልሆነው</u>** የቱ ነው?

    ሀ) 12 የ48 አካፋይ ነው፡፡ ሐ) 11 የ112 አካፋይ ነው፡፡

    ለ) 9 የ81 አካፋይ ነው፡፡ መ) 120 የ120 አካፋይ ነው፡፡

7. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል ትንሹ ብቸኛ ቁጥር ስንት ነው?

    ሀ) 3 ለ) 5 ሐ) 9 መ) 2

8. 840 በብቸኛ ትንትን ሲገለፅ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

    ሀ) $2^3 \times 3 \times 5 \times 7$ ሐ) $2 \times 3 \times 5 \times 7$

    ለ) $2 \times 3^2 \times 5 \times 7$ መ) $3 \times 5 \times 7$

9. የ32፣56 እና 48 ትልቁ የጋራ አካፋይ(ት.ጋ.አ) ስንት ነው?

    ሀ) 6 ለ) 10 ሐ) 8 መ) 16

10. የ60 እና 84 ትልቁ የጋራ አካፋይ(ት.ጋ.አ) 12 ቢሆን፣ ትንሹ የጋራ ብዜት (ት.ጋ.ብ) ስንት ይሆናል?

    ሀ) 24 ለ) 240 ሐ) 420 መ) 204

LIVEWORKSHEETS

11. መሪማ ለልደቷ ቀይ እና ነጭ አምፖሎችን በተመሳሳይ ሰዓት አበራች፤ ቀዩ በየ105 ሴኮንድ እና ነጩ በየ70 ሴኮንድ ቢበሩና ቢጠፉ ከስንት ሴኮንድ በኋላ አብረው መብራት ይጀምራሉ?

ሀ) 120 ለ) 210 ሐ) 201 መ) 420

12. $\frac{9}{12} = \frac{81}{መ}$ ቢሆን የ"መ" ዋጋ ስንት ይሆናል?

ሀ) 180 ለ) 810 ሐ) 801 መ) 108

13. ተማሪ ቅድስት የ6ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን በሒሳብ ትምህርት ከ40 ጥያቄ ውስጥ 36 ማርክ አገኘች፤የቅድስት ውጤት በመቶኛ ሲገለፅ ስንት ይሆናል?

ሀ) 90% ለ) 75% ሐ) 95% መ) 60%

14. 0.84 ወደ ክፍልፋይ ሲለወጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) $\frac{84}{50}$ ለ) $\frac{42}{25}$ ሐ) $\frac{21}{25}$ መ) $\frac{25}{21}$

15. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል **<u>ያልሆነው</u>** የትኛው ነው?

ሀ) $\frac{92}{100}$ =0.92 ለ) 75%=$\frac{3}{4}$ ሐ) $\frac{85}{100} = \frac{17}{20}$ መ) 62%=0.31

16. አቶ ባልቻ አንድ ኮምፒውተር በ25000ብር ገዝተው በ35000ብር ቢሸጡት፤የአቶ ባልቻ ትርፍ በመቶኛ ምን ያህል ነው?

ሀ) 60% ለ) 40% ሐ) 80% መ) 25%

17. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በ2015ዓ.ም 50000 ችግኞች ተተክለው 35000 ችግኞች ቢፀድቁ፤ የፀደቁት ችግኞች በክፍልፋይ ሲገለፅ ስንት ይሆናል?

ሀ) $\frac{7}{10}$ ለ) $\frac{5}{7}$ ሐ) $\frac{7}{5}$ መ) $\frac{1}{10}$

18. ከሚከተሉት ክፍልፋዮች ውስጥ ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደምተከተል የተቀመጠው የትኛው ነው?

ሀ) $\frac{3}{5}$፣$\frac{3}{4}$፣$\frac{1}{2}$፣$\frac{7}{8}$ ሐ) $\frac{1}{2}$ ፣$\frac{3}{5}$፣$\frac{3}{4}$፣$\frac{7}{8}$

ለ) $\frac{3}{4}$ ፣$\frac{7}{8}$፣$\frac{1}{2}$፣$\frac{3}{5}$ መ) $\frac{7}{8}$ ፣$\frac{3}{4}$፣$\frac{3}{5}$፣$\frac{1}{2}$

19. ከሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ ትልቁ የትኛው ነው?

ሀ) 0.96 ለ) $\frac{24}{25}$ ሐ) 0.7 መ) $3\frac{1}{2}$

20. ከሚከተሉት አስርዮሻዊ ቁጥሮች ውስጥ **<u>ከትልቅ</u>** ወደ ትንሽ በትክክል የተቀመጠው የትኛው ነው?

ሀ) 3.2፣2.1፣1.98፣ 1.89 ሐ) 2.1፣ 1.98፣ 3.2፣ 1.89

ለ) 1.89፣ 1.98፣ 2.1፣ 3.2 መ) 1.98፣3.2፣1.89፣2.1

21. $11\frac{7}{8}$ ወደ አስርዮሻዊ ቁጥር ሲቀየር ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) 0.875 ለ) 11.875 ሐ) 1.875 መ) 11

LIVEWORKSHEETS

22. $3\frac{2}{5} + 0.24$ ድምር ስንት ይሆናል?

ሀ) $\frac{25}{91}$ ለ) $\frac{90}{25}$ ሐ) $\frac{25}{9}$ መ) $\frac{91}{25}$

23. የ$2.25 - \frac{3}{4}$ ልዩነት ስንት ይሆናል?

ሀ) 2.75 ለ) 3.25 ሐ) 3 መ) 1.5

24. ሚሊዮን ከገቢያ 2.5ኪ.ግ ብርቱካን፣ $\frac{4}{5}$ኪ.ግ ሙዝ እና $2\frac{1}{5}$ኪ.ግ ማንጎ ይዞ ወደ ቤቱ ቢመለስ፣ሚሊዮን በአጠቃላይ ስንት ኪ.ግ ፍራፍሬ ገዛ?

ሀ) 5.5ኪ.ግ ለ) 55ኪ.ግ ሐ) 0.55ኪ.ግ መ) 11ኪ.ግ

25. ሀገሬ በጠዋት ተነስታ $4\frac{3}{4}$ኪ.ሎ ሜትር ለመሮጥ አቅዳ ነገር ግን 3.5ኪ.ሎ ሜትር ብትሮጥ የእቅዷን ለመሮጥ ስንት ኪ.ሎ ሜትር ይቀራታል?

ሀ) 1ኪ.ሜ ለ) 1.25ኪ.ሜ ሐ) 1.50ኪ.ሜ መ) 2ኪ.ሜ

26. ተማሪ መሐመድ በየቀኑ በሳይክል 20.5ሜትር ቢጓዝ፤በ6 ቀን ስንት ሜትር ይጓዛል?

ሀ) 120ሜትር ለ) 60.5ሜትር ሐ) 123ሜትር መ) 123.5ሜትር

27. የ$0.52 \times 3\frac{1}{2}$ ብዜት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) 0.182 ለ) 1.82 ሐ) 18.2 መ) 182

28. የ$8\frac{4}{5} \div 2.4$ ድርሻ ስንት ይሆናል?

ሀ) $\frac{110}{3}$ ለ) $\frac{11}{6}$ ሐ) $\frac{440}{5}$ መ) 22

29. 504000 በ10 ርቢ ሲገለፅ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) $5.4\times 10^5$ ለ) $54\times 10^5$ ሐ) $5\times 10^5$ መ) $5.04\times 10^5$

30. የአቶ ልዑልሰገድ መኪና በ$3\frac{3}{4}$ሰዓት ውስጥ 300ኪ.ሎ ሜትር ቢጓዝ፤የመኪናው ፍጥነት በሰዓት ስንት ነው?

ሀ) $70\frac{\text{ኪ.ሜ}}{\text{ሰዓት}}$ ለ) $80\frac{\text{ኪ.ሜ}}{\text{ሰዓት}}$ ሐ) $100\frac{\text{ኪ.ሜ}}{\text{ሰዓት}}$ መ) $75\frac{\text{ኪ.ሜ}}{\text{ሰዓት}}$

LIVEWORKSHEETS